# አስረኛ ትምህርት ከየካቲት 25 — መጋቢት 1 Mar 4— Mar 10

## መንፈስ ቅዱስ፣

## መጽሐፍ ቅዱስ እና ጸሎት

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዮሐ. 15:7፣ ማቴ. 7:7፣ መዝ. 66:18፣ ያዕ. 1:6-8፣ 1ዮሐ. 5:14-15፣ ሐዋ. 2:38።

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡- "እንዲሁ ም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል። ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ሀሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና።" (ሮሜ. 8:26-27)**

እውነተኛ መንፈሳዊነትና ጸሎት አብረው ይሄዳሉ። ብርቱ ጸሎተኝነት ሳይኖር እውነተኛ የመንፈሳዊ ህይወት ሊኖር አይችልም። አንድ ሰው ንስሐ ከገባ በኋላ ውሎ ሳያድር ሊተገብር ከሚገባው ነገር አንዱና ዋንኛው የተነቃቃ የጸሎት ሕይወት ነው። በጸሎታችን እንኳ ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ ብቻችንን አለመተዋችን በእርግጥ መልካም የምስራች ነው። ጸሎት ወደ

እግዚአብሔር ያቀርበናል--ሽቅብ ወደ አምላካዊው ህልዎት ያወጣናል። በእምነት የሚጸለይ ጸሎት ለተትረፈረፈው አምላካዊ ተስፋ ምላሽ እየሰጠን እንድንኖር ያስችለናል። እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት የሰጠንን የበረከት ተስፋዎች የራሳችን አድርገን ስንወስድ ህይወታችን የተለወጠ ይሆናል። እግዚአብሔር እንደ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልገንን ሁሉ ለማሟላት አብልጦ ይችላል (ፊልጵ. 4:19)። የእውነተኛ ጸሎትና የሐቀኛ መንፈሳዊ አስተሳሰብ ማዕከሉ ሁሌም ቢሆን እግዚአብሔርን ነው። እነዚህ ሁለቱም በአምላካዊው ቃል ላይ በጥልቅ የተመሰረቱ ናቸው።

የመንፈሳዊ ሕይወታችን መሰረት ካልጠነከረው ተሞክሮና ከግላዊ ስሜት ጋር የተያያዘ እንዲሆን መፍቀድ የለብንም ወይም ጥርጣሬ አዘል ማሰላሰልና ተመሰጦአዊ ልምድ ላይ ትኩረት ያደረገ ሊሆን አይገባም። በዚህ ፋንታ መንፈሳዊነታችን በቃሉ እንደ ተገለጠው--በመጽሐፍ ቅዱስ የተመራና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚከተል ሊሆን ይገባል። ከተኛንበት በመቀስቀስ በጸሎታችን የእግዚአብሔርን ሕልዎት እንድንናፍቅና አንዱ ሌላውን በጸሎት እንዲደግፍ የሚያስችለው መንፈስ ቅዱስ ነው።

*እሑድ የካቲት 26* *Mar 5*

**እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ጸሎት**

የኃይማኖተኛነቱን ካባ የደረቡ አያሌ ጸሎቶች ከበስተ ጀርባቸው አጠያያቂ ሰበበ ምክንያቶች ሊኖሯቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ምናልባት ብቻችንን መኖር ስለማንፈልግ ጌታ የሆነን ሰው ሕይወት ያተርፍ ዘንድ በጸሎት እናስበው ይሆናል፡፡ እጅግ በጣም አስፈላጊ ሚና እየተጫወትን መሆኑን ተከትሎ--በእግዚአብሔር ሥራ ስኬትና ክንውን እንድናገኝ እንጸልይ ይሆናል፡፡ ስለ አንድ ሰው መለወጥ እንጸለይ ይሆናል--ምክንያቱም የዚያ ሰው መለወጥ የእኛን ሕይወት ቀለል ሊያደርገው ስለሚችል፡፡ ጸሎታችን በአብዛኛው እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሳይሆን ነገር ግን እኛ የምንፈልጋቸውን ነገሮች ያማከለ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ጸሎት የትኩረት አቅጣጫ የተለየ ነው፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡-- ዮሐ. 15፡7፡፡ ጸሎታችን በየሱስ መኖራችንንና ቃሉ በእኛ ውስጥ መኖሩን ማካተቱ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? በየሱስ የማንኖር ከሆነ የጸሎታች አቅጣጫ ወዴት ያመራል?**

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በቅድሚያ እግዚአብሔርን መሻትና በአብሮነቱ ደስ መሰኘት እርሱ ከሚሰጠን ማንኛውም ነገር በላይ አብልጦ አስፈላጊ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሕይወታችን ቀዳሚውን ስፍራ ከወሰደ እርሱ የሚፈልገውን ለማድረግ እንመኛለን፡፡ የእርሱ ሀሳብ የልባችንን መሻት ይገራል፡፡ እግዚአብሔር አንዴ የጸሎታችን ማዕከል ከሆነ ከትክክለኛው የእርሱ ምልከታ አኳያ መጸለይ እንጀምራለን፡፡ መላውን ሕይወታችንን በእርሱ ዐይኖች መመልከት እንጀምራለን፡፡ እንዲህ ያለው ትክክለኛ አመለካከት ጸሎታችንን የከበረ ያደርገዋል፡፡

እግዚአብሔር የእኛ ነገር አይሆንለትም--በእጅጉ ያሳስበዋል፡፡ እግዚአብሔር--የጭንቀታችን፣ የፍርሃታችን፣ የምኞታችን፣ የስኬታችን፣ የደስታችን፣ የውድቀታችን--የማንኛውም የሕይወታችን ገጽታ አካል ለመሆን አጥብቆ ይመኛል፡፡ እነዚህን ሁሉ ነገሮች እንደ አንድ መልካም የልብ ወዳጅ ከእርሱ ጋር ልንነጋገርና ሁሉንም በእርሱ ዐይኖች መመልከት እንችላለን፡፡

ሕይወትን በሚቀይረው አምላካዊ ህልዎት ፊት እንደ መቅረባችን--ጸሎት እግዚአብሔርን ሳይሆን ነገር ግን እኛን ይቀይራል፡፡

“ጸሎት እግዚአብሔርን እንደ ወዳጃችን ቀርበን ልቡን የምንከፍትበት ቁልፍ ነው፡፡ የምንገኝበትን ሁናቴ ማሳወቃችን እርሱን መቀበል እንድንችል እንጂ እርሱ ያን የማይገነዘብ ስለሆነ አይደም፡፡ ጸሎት እግዚአብሔርን ወደ እኛ አያወርደውም ይልቁንም እኛን ወደ አምላካዊው ሕልዎት ያወጣናል፡፡”–Ellen G. White, Steps to Christ, p. 93.

ከላይ በትምህርተ ጥቅስ የቀረበው ብርቱ ሃሳብ ጸሎት ለእኛ የሚያደርገውን ነገር በተጨባጭ አስቀምጦአል፡፡ ጸሎት--አምላካዊውን ጸጋ፣ ኃይልና ሕልዎት  በህይወታችን የምንቀበል ያደርገናል፡፡ ይብዛም ይነስም--ጸሎት ምን ያህል በተጨባጭ ወደ እግዚአብሔር እንደሚያቀርበን ያላስተዋለ ይኖር ይሆን?

**ስለ ራስዎ የጸሎት ሕይወት አሰብ ያድርጉ፡፡ ሰለ ምን ይጸልያሉ? መቼ ይጸልያሉ? ለምን ይጸልያሉ?... መልስዎ ስለ ሚገኙበት መንፈሳዊ ሁናቴና ከእግዚአብሔር ጋር ስላሎት ግንኙነት ምን ይነግሮታል? ምን ዓይነት ለውጥ ሊያደርጉ ይገባል?**

## እግዚአብሔርን መጠየቅ፡ የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጸሎት መሰረት

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡-- ማቴ. 7፡7፡፡ ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር ከመቀበላችን አስቀድሞ ልንጠይቀው ይገባል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የሚያውቅ ከመሆኑ አኳያ መጠየቃችን ለምን አስፈለገ?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

እግዚአብሔርን መጠየቃችን የልባችንን ምኞትና በእግዚአብሔር ላይ ያለንን መታመን ይገልጻል፡፡ እርዳታውንና እገዛውን መሻታችን በጸሎት ወደ እርሱ እንድንቀርብ ያስችለናል፡፡ እግዚአብሔርን ጠየቅነው ማለት ስለ እኛ በሕይወታችን ንቁ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ በይፋ ፈቀድንለት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር እንዲጠየቅ ይፈልጋል፡፡ ጸሎታችንንና ልመናችንን ወደ እርሱ እንድናቀርብ አጥብቆ ይመኛል፡፡ ካልጠየቅነው ቃል የገባልንን ስጦታዎች መቀበል አንችልም፡፡ "ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ ምክንያቱም የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልግም ያገኛል፤ በር ለሚያንኳኳም ይከፈትለታል፡፡" (ሉቃስ 11:9-10)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ማር. 11:24፣ 1ዮሐ. 5:14-15፣ መዝ. 66:18፡፡ በጸሎት ምንም ጥያቄ አለማቅረብ ለእግዚአብሔር በጣም ከባድ የሆነው ለምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ለጋስነትና ከተትረፈረፈ በጎነቱ ሊሰጠን እንደሚወድ ማወቃችን መልካም የሆነው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዲሰማ ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

እግዚአብሔር የምንፈልገውን እንዲያሟላልን በእርግጠኝነት ልንጠይቀው እንችላለን፡፡ በእርሱ ፊት እጅግ መናኛ ወይም የማያስፈልግ የሚባል ዓይነት ልመና የለም፡፡ ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር አዳጋች የሚሆንበት ከባድ ልመና የለም፡፡ እርሱ ሁሉንም ነገር ማድረግ የሚችል ኃያል አምላክ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የቀረበውን እያንዳንዱን ተስፋ የኔ ነው ልንልና እንደ በጎ ፈቃዱ ቃል የገባቸውን ስጦታዎች ልንቀበል እንችላለን (2ቆሮ. 1:20)፡፡

የምንጠይቀውን ለመቀበል ሌሎች ሊሟሉ የሚገባቸውም ነገሮች አሉ፡፡ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት ሙሉ ለሙሉ ፈቃደኝነት ከጎደለንና ልመናችን ራስ ወዳዱንና ኃጢአተኛውን ምኞት ብቻ የሚያንጸባርቅ ከሆነ እግዚአብሔር መልስ ሊሰጠን አይችልም (ኢሳ. 59:1-2)፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመከተልና እርሱን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ልብ ለልመናችን መሰማት አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ "አምላካዊው ስጦታዎች ሁሉ ለእርሱ የመታዘዛችንን ቅድመ ሁኔታዎች ታሳቢ አድርገው የሚሰጡ ናቸው፡፡"–Ellen G. White, Christ's Object Lessons, p. 145. የእግዚብሔርን ለጋስነት ተረድተን በድፍረት በፊቱ ልንቀርብ እንችላለን፡፡ "ጌታ ምንም ሊቀበል እንደማይችል በማይጠብቅ የማያንን ልመና ሊከብር አይችልም፡፡ እያንዳንዱ አማኝ በትህትናና በተረጋገጠ ተስፋ ወደ ጸጋ ዙፋኑ ይቅረብ፡፡"–Ellen G. White, Signs of the Times, Aug. 7, 1901.

## እምነት፡- የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጸሎት መሰረት

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡-- ማር. 11፡24። የሱስ ከመጠየቅ በተጓዳኝ የሚጠቅሰው ሌላ ነገር ምንድን ነው?

መጠየቅ ብቻውን በቂ አይደለም። በጸሎታችን ላይ ሊቀርብ የሚገባ ሁለተኛ አስፈላጊ ነገር ያለ ሲሆን ይኸውም እምነት ነው። የዕብራውያን መጽሐፍ “ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም” (ዕብ. 11፡6) ይለናል። ልጅ አባቱን እንደሚጠይቅ በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክከን ከተሰጡን ከሶስት ሺ በላይ ተስፋዎች የትኛውንም ለመቀበል መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከፍተን እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እንዲፈጽም በስሙ ስንጠይቀው--ምርጥ የሆነውን ሁሉ እንደሚያደርግልን በማመን ሊሆን ይገባል።

ጥቅሱን ያንብቡ፡-- ያዕ. 1፡6-8። እምነት የጎደለውን ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጸው እንዴት ነው? እግዚአብሔር እንደሚሰጠን ቃል የገባልንን ስጦታ ለመቀበል እምነት እንደ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠው ለምንድን ነው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------

ወደ እግዚአብሔር የምንመጣ ከሆነ የአምላካዊውን ሕልዎት ልንቀበልና አጥብቀው የሚሹትን እንደሚሸልም ልናምን ይገባል። ኃይል ያለው ጸሎት እግዚአብሔር ልመናን እንደሚሰማ የሚያምን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን መልስ መስጠት የሚችለው እንደ መለኮታዊ ፈቃዱ መሆኑን አምኖ ይቀበላል።

ማመንና መታመን ተያያዥነት እንዳላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። በአንድ ሰው ላይ አመኔታ የምናሳድረው ታማኝ መሆኑን ስናውቅ ብቻ ነው። የምንጠራጠር፣ የምንወላውል ወይም የምናመነታ ከሆነ እግዚአብሔር ቃል ከገባው ውስጥ አንዳች ነገር ለመቀበል መጠባበቅ የለብንም። ማመን--እግዚአብሔርን በተናገረው መሰረት መቀበል ነው። ይህ ማለት--ስሜታችን አይሆንም ቢለን እንኳ--በእግዚአብሔርና እርሱ በሰጠው ተስፋ ላይ መተማመን ነው። “እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው” (ዕብ. 11፡1)። እግዚአብሔር የተናገረውን እኛ በማመናችን ምክንያት እምነት እርሱ ከሰጠው ተስፋ ጋር አጥብቆ የተያያዘ ነው (ዕብ. 6፡18)። እግዚአብሔር ትናንት፣ ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው (ዕብ. 13፡8)። ለእግዚአብሔር አንዳችም የሚሳነው ነገር እንደ ሌለ እምነት ያውቃል (ሉቃ. 1፡37)። እምነት የመለኮታዊውን ግምጃ ቤት ደጃፍ ወለል አድርጎ ይከፍታል። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የወንዶችንና የሴቶችን ልብ እየነካ ለአምላካዊው ቃል ታማኝ እንዲሆኑ ያደርጋል። በእምነት የምንጸልየው ጸሎት ሁሉን የሚችለውን ኃያል አምላክ እጆች ማንቀሳቀስ ይችላል።

በእምነት እየጠነከሩ እንዲሄዱ ሊረዳዎ የሚችለው ምንድን ነው? የተለየ ዕጦት ሲገጥሞት በእርሱ ፈቃደኝነትና ችሎታ ላይ በመተማመን የለመኑትን እንዲቀበሉ ሊያደርጎት የሚችለው የትኛው የየሱስ ተስፋ ነው?

*ረቡዕ  የካቲት 29*  *Mar 8*

## የእግዚአብሔርን ተስፋ አምኖ መቀበል፡ የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጸሎት መሰረት

ጸሎት ያደረግንበትን ነገር በእምነት መቀበል የማንችል ከሆነ እምነታችን በሙሉ ከንቱ ነው ማለት ነው።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- 1ዮሐ. 5፡14-15። የምንጸልየውን ጸሎት እግዚአብሔር እንደሚሰማና የልመናችንን ምላሽ ማግኘት እንደምንችል ልበ ሙሉ ያደረገን ምንድን ነው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በሶስተኛ ደረጃ የተቀመጠው የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጸሎት ገጽታ--መቀበል ነው። እግዚአብሔርን ከጠየቅንና በሰጠን ተስፋዎች ላይ እርግጠኞች ከሆንን በኋላ ተስፋውን እንደሚፈጽም አምነን መቀበል ይኖርብናል። ለእግዚአብሔር የምስጋና ምላሽ በማቅረብ የለመንነውን እንዳገኘን--አምነን መቀበል የኛ ፋንታ ነው። በዚህም ተስፋዎቹ በልባችን ውስጥ ተጨባጭ ስፍራ ይይዛሉ። “እግዚአብሔር እንደሚሰጠን ቃል ለገባው ለማንኛውም ስጦታ ልናመሰግነውና ስጦታውን እንደ ተቀበልን አድርገን በማመን የአጸፋ ምስጋና ልናቀርብለት የተገባ ነው።”–Ellen G. White, Education, p. 258.

የሱስ በሉቃ. 8፡11 የእግዚአብሔርን ቃል ከዘር ጋር ሲያነጻጽር ይታያል፡፡ የፖም ዛፍ ምንጩ የፖም ፍሬ እንደመሆኑ በተመሳሳይ የእግዚአብሔርም ስጦታ ምንጭ እርሱ የሰጠው ተስፋ ነው። አምላካዊውን ተስፋ የራሳችን አድርገን በመቀበል ምስጋና ስናቀርብ--በእርግጥም በተስፋ የሰጠንን ያንን ነገር የግላችን እናደርጋለን። በተስፋ የተሰጠንን ስጦታ ገና ሳናየውና ሳናጣጥመው አስቀድመን በእምነት እንቀበላለን።

በዮሐ. 11 የምናነበው የአልዓዛር ከሞት የመነሳት ምሳሌ የሱስ በዚህ መንገድ የጸለየውን ጸሎት በጉልህ ያሳያል። የሱስ በዚህ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን ሊሆን እንደሚችል በትክክል ያውቅ ነበር። የሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ፈቃደኛና ታዛዥ እንደ ነበር ዮሐ. 11፡11 ይነግረናል። እንዲሁም በዮሐ. 11፡39-41 ምንም እንኳ አልዓዛር ገና በመቃብር ቢሆንም ነገር ግን እንደሚያስነሳው በማመን አብን አስቀድሞ እንዳመሰገነ እናነባለን። የሱስ ለአብ ምስጋና እንዳቀረበ በቅጽበት ውስጥ የልመናውን ሙሉ ምላሽ አገኘ። እንደ እግዚአብሔር ልጅነታችን በአምላካዊው ተስፋ ልንኖር የግድ ነው። ምንም እንኳ ለሁሉም ነገር ማብራሪያ መስጠት ባንችልም ነገር ግን የሰጠንን ተስፋዎች አምነን ልንቀበላቸው እንችላለን።

“ጌታ ‘በመከራ ጊዜ ወደ እኔ ጨኽ’--መዝ. 50፡15 ይለናል። ግራ መጋባታችንንና የሚያስፈልገንን ሁሉ በፊቱ በማቅረብ መለኮታዊ እርዳታውን እንድንቀበል ጥሪ ያደርግልናል። በጸሎት እንድንተጋ ያዘናል። ማንኛውም ችግር ሲደርስብን ቅን የሆነውንና ልባዊ ልመና እናቅርብለት። ጽኑው ጸሎታችን በእግዚአብሔር ላይ ያለንን ጠንካራ መተማመን የሚያሳይ ይሁን። የሚያስፈልገን ነገር እንዲሟላልን የምናቀርበው ያላሰለሰ ልመና የሰማዩን አባታችንን ልብ ይነካል።”–Ellen G. White, Christ’s Object Lessons, p. 172.

ሁሉንም ነገር በጸሎት በእግዚብሔር ፊት ማቅረብ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

*ሐሙስ  የካቲት 30*  *Mar 9*

## ለመንፈስ ቅዱስ መጸለይ

**እዚህ ሁለት ጥቅሶች ማለትም-- ኤፌ. 3፡16 እና ሐዋ. 2፡38 መንፈስ ቅዱስን በሕይወታችን ስለመቀበል ምን ይነግሩናል?**

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ልንጸልይባቸው የሚገቡ አያሌ ነገሮች ቢኖሩም ነገር ግን በዚህ በምንኖርበት በአደጋ የተሞላ ዘመን አንድ በጣም የሚያስፈልገን ነገር አለ--መንፈስ ቅዱስ! የሱስ ሊሰጠን የሚችለው እጅግ የላቀ ስጦታ ይህ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መንፈስ ቅዱስን የመስጠቱን ያህል ሊሰጥ የሚችለው የበለጠ ነገር ሊኖር አይችልም፡፡ በዚህ ስጦታ ላይ መታከል የሚችል አንዳች ነገር አይኖርም (ደግሞስ በመለኮት ላይ ምን ሊታከል ይችላል?)፡፡ እርሱ በሕይወታችን ውስጥ በሚሠራው ሥራ ለእኛ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች በሙሉ ይሟሉልናል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ በረከት ሌሎች አያሌ በረከቶችንም አጭቆ ከተፍ ይላል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ ብርቱ እንቅፋት ግን አለ፡፡ እንቅፋቱ--እኛው ስንሆን ይኸውም መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ዝግጁ ያለመሆናችን ነው፡፡

በአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነው ሁሉ በመጀመሪያ ንስሐ መግባትና ህይወታችንን ለየሱስ ማስገዛት እንደሚኖርብን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ በእርግጥ ይህ ገቢራዊ መሆን የሚችለው በቅድሚያ መንፈስ ቅዱስ በልባችን መነሳሳት ሲያመጣ ብቻ ነው፡፡

ለመንፈስ ቅዱስ ማነሳሳት ምላሽ ስንሰጥ ለኃጢአታችን ንስሐ እንገባለን፡፡ ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን እየሠራ የመሆኑ የመጀመሪያ ፍሬ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከማንኛውም ጽድቅ ከጎደለው ህይወት ያነጻን ዘንድ ራሳችንን ዝቅ በማድረግና በእምነት ኃጢአታችንን መናዘዝ ይኖርብናል፡፡ በኃጢአት አዘቅት ውስጥ ጭልጥ ብለን እንደ መውደቃችን--እግዚአብሔርና የእርሱ ጸጋ ምን ያህል በሕይወታችን ሊያስፈልገን እንደሚችል ማስተዋል ይኖርብናል፡፡ ያለ እርሱ--የጠፋን፣ በኃጢአታችን የሞትንና ለዘላለማዊ ኩነኔ የታጨን ነን፡፡

ሳንታክት በመጸለይ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጠን የገባልንን የቃል ኪዳን ቅድመ ሁኔታ እናሟላለን፡፡ ይህ ሲሆን ከእኛ የሚጠበቀው እግዚአብሔርን መጠየቅ ብቻ ይሆናል፡፡ እርሱ ደግሞ መንፈሱን በደስታ ይሰጠናል፡፡ "ምድራዊ ወላጆች መልካም ስጦታዎችን ለልጆቻቸው ከሚሰጡት ይልቅ ሰማያዊው ወላጅ መንፈስ ቅዱስን ለሚጠይቁት ለመስጠት የበለጠ ፈቃደኛ ነው፡፡"–Ellen G. White, Ye Shall Receive Power, p. 284.

ከሌሎች መንፈሳዊ ነገሮች በተጓዳኝ የሚሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የመጨረሻ ስጦታ አይደለም፡፡ መንፈስ የሚሰጠን የሱስ ይበልጥ ክብሮ በጉልህ እንዲታይ ለማድረግ፣ የክርስቶስ ጸባይ በሕይወታችን ሰርጾ የእርሱ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን በማጎልበት ሌሎችን ለማገልገል ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ማንኛውም በግልም ሆነ በጉባዔ የሚደረግ መንፈስን ከየሱስ ክርስቶስ በላይ ከፍ የሚያደርግ አምልኮ ፍጹም የተሳሳተ ነው፡፡ ሁላችንም በየሱስ "አማካይነት በአንዱ መንፈስ ወደ አብ መቅረብ እንችላለን" (ኤፌ. 2:18)፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሱስ ሊሰጠን ከሚችለው ስጦታ ሁሉ የበለጠ የሆነው ለምንድን ነው? መንፈስ ቅዱስ በተጨባጭ በሕይወትዎ ያደረገውን የሚገልጸው የግል ተሞክሮዎ ምን ይመስላል? ሕይወትዎ ያለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ምን ያህል የተለየ ሊሆን ይችል ነበር?

## ተጨማሪ ሃሳብ:-

Read Ellen G. White, “Asking to Give,” pp. 139-149, in Christ’s Object Lessons. For a helpful collection of encourag-ing promises read Ellen G. White, God has Promised (Washington, D.C.: Review and Herald, 1982).

ጸሎት ከኃይል ምንጭ ጋር የሚያገናኘን መስመር እንደመሆኑ ያለ ጸሎት ሕይወት መንፈሳዊ ኃይል ሊኖረን አይችልም። ያለ ጸሎት ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር መሰረታዊ ግንኙነት መፍጠር አንችልም። የጸሎት ሕይወት ከሌለን--አምላካዊውን ኃይልና ከፍ ያሉትን የስጦታዎቹን ተስፋ የተራቆትን “ሃይማኖታዊ መልክ” ብቻ የያዝን ባዶ ማድጋዎች መሆናችን ሳይታለም የተፈታ ነው። እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ እንደሚሰጥ የሚያወሱ ግሩም ተስፋዎችን በዚህ ሳምንት ጥናታችን በተጨባጭ ለመመልከት ሞክረናል። ሆኖም እግዚአብሔር የሰጠንን ችሎታዎች ተጠቅመንና እርሱ ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በተቻለ አሟልተን ጸልየንባቸው--መልስ ሳናገኝ የቀረንባቸው ጉዳዮችስ? “ልመናዎ አፋጣኝ ምላሽ ያላገኘ ሆኖ ቢሰማዎ--ተስፋ አይቁረጡ። ጸሎት በአብዛኛው ከምድራዊ ነገሮች ጋር የተደባለቀ መሆኑን ጌታ ይመለከታል። ሰዎች የሥጋዊውን ፈቃድ ለሚያረካውና ደስ ለሚያሰኘው ምኞት እውን መሆን ስለሚጸልዩ--ጌታ እነርሱ በሚጠብቁት መንገድ ልመናቸውን አያሟላም። ለእነርሱ በትክክል የሚያስፈልጉትን ነገሮች ይበልጥ በግልጽ መመልከት እስከሚችሉ--በአስቸጋሪ ሁናቴዎች ውስጥ በመውሰድ ይፈትናቸዋል። እርሱ ሰብዓዊውን ፍጡር አርክሶ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲነፍግ መንስኤ መሆን የሚችለውን ፍላጎት የሚያስደስት ነገር አይሰጥም። የሥጋን ከንቱ ምኞት ለማርካትና ራስን ከፍ ለማድረግ የሚቀርበውንም ልመና አይሰማም። ሁሉንም ነገር በተቀደሰ ፈቃዱ ስር በማስገዛት በታዛዥና በተጸጸተ ልብ ወደ እግዚአብሔር ልንመጣ ይገባል።”–Ellen G. White, In Heavenly Places, p. 89.

## የመወያያ ጥያቄዎች

- ጸሎት በመላው መንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ ተጽእኖ ማሳደር የሚችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ማለትም--አዘውትረው በሚጸልዩበት ወቅት በራስዎ ላይ የተመለከቱት ተጽእኖ ምን ይመስላል? ሲጸልዩና ሳይጸልዩ ምን ዓይነት ልይነቶችን ማስተዋል ችለዋል?
- ለታመመ ህጻን ፈውስ ከመሻትና ከመሳሰሉት በተጓዳኝ አብልጦ ጸልዮና ተስፋ አድርጎ ነገር ግን ምንም ምላሽ ላላገኘው ሰው ምን ሊሉት ይችላሉ? የእግዚአብሔርን ታማኝነት በእንደነዚህ ዓይነት አስቸጋሪ ሁናቴዎች ውስጥ እንዴት መማር እንችላለን?
- በጸሎት ዙሪያ ያሎትን የግል ተሞክሮና ጸሎት ለእርስዎ ምን ዓይነት ትርጉም እንዳለው ያካፍሉ። የጸሎትን ዓላማ ለማስተዋል በትግል ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ወገኖችን ሊረዳ የሚችል ስለ ጸሎት የተማሩት ነገር ምንድን ነው?
- ጸሎት እንዴት እንደሚሠራ ሙሉ ለሙሉ ባናውቅም፤ መጸለይ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?